የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፫
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፫ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 43
ADDIS ABABA 30th June, 2009

ማውጫ

CONTENTS

አዋጅ ቁጥር ፮፻፴፮/፪ሺ፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ እና በሕንድ መንግሥታት መካከል የጋራ ሚኒስትሮች ኮሚሽን ለማቋቋም የተፈረመውን ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ … ገጽ ፬ሺ፯፻፵፪

Proclamation No. 636/2009

Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of India on the Establishment of Joint Ministerial Commission Ratification Proclamation……. Page 4742

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፴፮/፪ሺ፩

## በኢትዮጵያ እና በህንድ መንግሥታት መካከል የተፈረመውን የሚኒስትሮች የጋራ ኮሚሽን ማቋቋሚያ ስምምነትን ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በሕንድ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል እ.ኤ.አ. ጁን ፭ ቀን ፪ሺ፯ በአዲስ አበባ ኢትዮጵያ ሚኒስትሮች የጋራ ኮሚሽን ለማቋቋም ስምምነት ላይ የተደረሰ በመሆኑ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፳፯ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ እና የህንድ መንግሥታት የሚኒስትሮች የጋራ ኮሚሽን ማቋቋሚያ ስምም ነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፴፮/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 636/2009

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF INDIA ON THE ESTABLISHMENT OF JOINT MINISTERIAL COMMISSION

**WHEREAS,** the Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of India for the establishment of Joint Ministerial Commission was signed in Addis Ababa, Ethiopia on the 5th day of June 2007;

**WHEREAS,** the House of peoples' Representa-tives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 4th day of June, 2009;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of India on the Establishment of Joint Ministerial Commission Ratification Proclamation No. 636 /2009".

## ፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በህንድ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተፈረመው የሚኒስትሮች የጋራ ኮሚሽን ማቋቋሚያ ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. <u>የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማስፈፀም ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

## ፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፫ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. <u>Ratification of the Agreement</u>

The Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of India on the Establishment of Joint Ministerial Commission signed in Addis Ababa, Ethiopia on the 5th day of June 2007 is hereby ratified.

## 3. <u>Power of the Ministry of Foreign Affairs</u>

The Ministry of Foreign Affairs is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Agreement.

## 4. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 30th day of June, 2009**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**